የሰ/መ/ቁ. 152523

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋአህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርሃኔ ተካ -የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ እስጥፋኖስ አለማየሁ } ጠበቃ ደረጀ ወዳጆ ቀረቡ 2ኛ ተጠሪም ቀረቡ

2 ወ/ሮ ጽዮን አለማየሁ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ከሥር 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ጋር በመሆን የአሁን ተጠሪዎችን ጨምሮ በሥር ሶስት ተጠሪዎች ላይ ታኅሳስ 12 ቀን 2002 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ውርስ እንዲጣራ ጠይቀው ውርሱ ተጣርቶ ቀርቦ የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ፍርድ ቤቱ በ20/10/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ያፀደቀው ሲሆን በዚህ ውሳኔ የሥር አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ጠይቀው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 156996 በሆነው በ21/9/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የሥር ፍርድ ቤት 1ኛ አመልካች /የአሁን አመልካች/ እና የሥር 3ኛ ተጠሪ /የዚህ ሰበር ተከፋይ ያልሆኑት/ ከሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚስትነት

ግንኙነት መሆን አለመሆኑን በተገቢው ማስረጃ እንዲያረጋግጥ፣ እንዲሁም የውርስ ሀብት ናቸው የተባሉት በላሊበላ እና በቢሾፍቱ ከተማ አሉ የተባሉ ቤቶች የውርስ ሀብት መሆናቸውን በማረጋገጥ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት መዝገቡን መልሶታል፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የሥር 1ኛ አመልካች /የአሁን አመልካች/ ሚስትነት ስንመለከት በቀረበው የፍርድ ቤት ውሳኔ በ17/6/2002 ዓ/ም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ 1ኛ አመልካች ሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ሚስት አለመሆናቸውን በማረጋገጥ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ውሳኔ ያፀናው በመሆኑ 1ኛ አመልካች ሚስት አለመሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ የሥር 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ በ16/6/1997 ዓ/ም በተሰጠ ውሳኔ የሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ሚስት መሆናቸው  የተረጋገጠ ሲሆን ነገር ግን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ህዳር 12 ቀን 1997 ዓ/ም በዋለው ችሎት በ16/6/1997 ዓ/ም የሰጠውን  ውሳኔ  የሻረው በመሆኑ የሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ሚስት ስለመሆናቸው ተጠሪ ሌላ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ 3ኛ ተጠሪ የሟች ሚስት አይደሉም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ስለሆነም 1ኛ አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ የሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ሚስቶች ስላልሆኑ በሟች የውርስ ሀብት ላይ ድርሻ የላቸውም በማለት ከደመደመ በኃላ የሟች ንብረቶች የሆኑትን በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በ474 ካሬ ሜትር ላይ የሚገኘውን የቤት ቁጥር 267፣ በላሊበላ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 01 የሚገኘውን ቤት እና በአዲስ አበባ ከተማ በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20 ውስጥ የሚገኘውን የቤት ቁጥር 206 የሆነውን መኖሪያ ቤት አራቱም የሟች አቶ  አለማየሁ  አብርሃ ወራሾች እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ተዘግቶባቸዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በውሳኔው ላይ ተፈጽሞብኛል ያሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን ጥር 15 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች ከሟች ጋር ለረዥም ዓመታት አብረው በመኖር ልጅም ወልደው እየኖሩ ባለበት ሁኔታ ከሟች ጋር የባልና ሚስት ግንኙነት የለም በመባሉ ብቻ አብረው በኖሩበት ወቅት ያፈሩትን ንብረት የመካፈል መብት የላቸውም የመባሉ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል በቀን 17/7/2010 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የአመልካች ጠበቃም ሚያዚያ 8 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በቀረበው ጉዳይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩ እንደሚከተለው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ተመርምሯል፡፡ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር አስቀድሞ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ የአሁን አመልካች ከሌሎች ሁለት ይግባኝ ባዮች ጋር በመሆን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ሲሆን የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሥር ፍርድ ቤት 1ኛ አመልካች /የአሁን አመልካች/ እና የሥር 3ኛ ተጠሪ ከሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚስትነት ግንኙነት መሆን አለመሆኑን በተገቢው ማስረጃ እንዲረጋገጥ በማድረግ፣ የውርስ ሀብት ናቸው የተባሉት በለሊበላ እና በቢሾፍቱ ከተማ አሉ የተባሉ ቤቶች የውርስ ሀብት መሆናቸውን ከተገቢው የአስተዳደር አካል እንዲረጋገጥ በማድረግ እና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በማስቀረብ እና በመስማት ተከራካሪዎች በውርስ ሀብቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ እና የውርስ ሀብቱን በመለየት አግባብ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ሲል በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት መልሷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በተመለሰለት አኳኋን አጣርቶ ውሳኔ ሰጥቷል ወይ? የሚለው ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ከተመለሰለት በኃላ የአሁን አመልካች የሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ሚስት አለመሆናቸው አስቀድሞ አዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተወሰነ በመሆኑ ሚስት አይደሉም ሲል ወስኗል፡፡ ነገር ግን የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለሥር ፍርድ ቤት ሲመልስ የአሁን አመልካች "ከሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ጋር ያለው ግንኙነት የሚስትነት ግንኙት መሆን አለመሆኑን በተገቢው ማስረጃ እንዲረጋገጥ በማድረግ" እንዲወስን የሚል ነው፡፡ ይህ ውሳኔ ሲሰጥ የአሁን ተጠሪዎች የክርክሩ ተከፋይ የነበሩ ሲሆን ጉዳዩ አስቀድሞ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ ለሥር ፍርድ ቤት በተያዘው ጭብጥ በመሠረት እንዲጣራ መመለስ የለበትም በማለት ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔውን አላሻሩም፡፡ በሌላ አነጋገር የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የአሁን ተጠሪዎች ተቀብለውታል ማለት ነው፡፡ አንድ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ በይግባኝ ካልተሻረ በስተቀር ፀንቶ እንደሚቆይ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 212 ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ከከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በተመለሰው አግባብ ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ መወሰን ሲገባው የሥር ፍርድ ቤት አስቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ በመጥቀስ አመልካች የሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ሚስት አይደሉም ሲል የደረሰው ድምዳሜ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 72189 ላይ በበላይ ፍ/ቤት ትዕዛዝ አንድን በነጥብ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰ ጉዳይ አይቶ እልባት እንዲሰጥበት የተላለፈለት ፍ/ቤት የተመለሰውን ጉዳይ የበላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ መሠረት በማድረግ በአግባቡ ውሣኔ ለመስጠት ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን ይህ ትርጉም ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ መሠረት በየትኛውም ደረጃ በሚገኙት ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ያለው ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከተው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በኮ/መ/ቁ. 156996 ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በመለሰው ትዕዘዝ መሠረት ተጣርቶ የተሰጠ ውሳኔ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔም ሆነ የከፍተኛ ፍርድ

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግን ዛቤ እ ን ጂ
ለ ፍርድ አ ፈ ጻ ጸ ምዓ ላ ማ አ ያ ገ ለ ግልም!

ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

# ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 62378 በቀን 11/7/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትበኮ/መ/ቁ. 194771 በቀን 16/02/2010 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 156996 ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተሰጠው ውሳኔ ለሥር ፍርድ ቤት በተመለሰው መሠረት የሚስትነት ጉዳይ መጣራት ሲገባው አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ተጠቅሶ አመልካች የሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ሚስት አይደሉም መባሉ ተገቢ አይደለም ተብሎ ተሽሯል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች "ከሟች አቶ አለማየሁ አብርሃ ጋር ያለው ግንኙነት የሚስትነት ግንኙት መሆን አለመሆኑን በተገቢው ማስረጃ እንዲረጋገጥ በማድረግ"እንዲወስን ሲል ከመለሰው " የሚስትነት ግንኙነት " የሚለው ትርጉም በሚያገኝ መልኩ ተጣርቶ እንዲወሰንና ይህ ከተጠራ በኃላ የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. የሟች ወራሾች አራቱ ናቸው የተባለው የውሳኔ ክፍል በአግባቡ ስለሆነ ፀንቷል፡፡
5. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ግንቦት 01 ቀን 2010 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ አስቀድሞ ለተጻፈለት አካል ይጻፍ፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይደረሳቸው፡፡
8. ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገ ለግልም!